LAW vs Grace



UNDER WHICH ARE YOU LIVING?

Beimnet Yalmzewd 2012EC
0964324390

Law Vs Grace




ገላትያ 3-1፤

የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው???

♥ Law Vs Grace ♥

♥ሕግ ኦና ፀጋ ♥



By Beimnet yalmzewd 2011 EC
0964324390

ሕግ እና ፀጋ

♥እንግዲህ እንዲህ ያለ ተስፋ ካለን፤እጅግ ገልጠን እንናገራለን
2ቆሮንቶስ 3፡12፤♥

- በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን
- በሙሴ እና በክርስቶስ
- በሕግ እና በፀጋ
- በእንስሶች ደም እና ክቡር በሆነው በኢየሱስ ደም መካከል ያለውን

ልዩነት ያልተረዳ እና ጠንቅቆ የማያውቅ ሰው ብዙ እውነቶችን ያበላሻል።

2ጢሞ 2፡15

የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፤ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።

ሕግ እና ፀጋ

ሕግ የተሰጠበት አላማ

፩፡-ሀጢአት እንዲታወቅ

ሮሜ 7 (Romans)

7፤ እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፡— አትመኝ፥ ባለለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።

19፤ አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤

20፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

ሕግ እና ፀጋ

፪፡-ሀጢአት እንዲገለጥ

ሮሜ 7 (Romans

8፤ ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።

13፤ እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።

ሕግ እና ፀጋ

፫፡-ሀጢአት በሀጢአትነቱ እንዲገለጥ እና ሰወች ሁሉ ሀጢአተኝነታቸውን እንዲያውቁ እናም በራሳቸው ፅድቅ መታመን ትተው ወደ ተገለጠው ወደ እግዚአብሔር ፅድቅ ፊታቸውን አንዲያዞሩ፤እንዲታመኑበትም ጭምር ነው።

ሮሜ 3 ፡-10፤ እንዲሀ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦—11፤ ጻድቅ የለም አንድ ስንኪ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥

19፤ አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤20፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

ሮሜ 3 (Romans)21፤ አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥

27፤ ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።

ፀጋ

- **ፀጋ** ማለት ለማይገባው ማንነት የተሰጠ ነጻ ስጦታ ነው።
- ይህም እንዲሁ በእግዚአብሔር ደግነት ላይ ተመስርቶ ሀጢአተኛ ለሆነው ሰው ***ያለምንም ምክንያት*** ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሳ **ብቻ** የሚሰጠው ስጦታ ነው። **ሮሜ 3፥23-24**
- **የፀጋ ስጦታ** ማለት ተቀባዩ ከራሱ ተገቢነት የሚቀበለው ሳይሆን እንዲሁ የተሰጠው ነው ::
- **ከዛሬ 2000 ዓመት በፊት የእግዚአብሔር ፀጋ ይኸውም በህግ ስራ ሊጸድቅ ያልቻለውን ሰው የሚያድን እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ምድር ተገልጧል። ይህም ፀጋ ሰዎችን ሁሉ ማዳን ይችላል።**

ዮሐ 1፥14-17

- **ሰው ለመዳን ከፈለገ የግድ ይህንን ጸጋ በእምነት መቀበል ይኖርበታል።**

ሮሜ 5 ፥ 2 ፣

ኤፌ 2 ፥ 8

ፀጋ

- **በጸጋ** ማመን ማለት እኛ መስራት የሚጠበቅብንን ስራችንን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሰራልን ፣ ሀጉ ከእኛ የሚጠይቀውን እርሱ እንደፈጸመው ፣ እንዲሁም በእኛ ሳይሆን በራሱ በክርስቶስ ስራ ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበን በማመን መቀበል ነው።

  ኤፌ 2 ፡ 4 – 8 ፤ ኤፌ 2 ፡ 18

- ሰዎች ሁሉ በዚህ **ጸጋ** መዳን ይችላሉ።

  ቲቶ 2

- የእግዚአብሔር ጽድቅ እንጂ የሰው ጽድቅ አያድንም። ስለዚህ በክርስቶስ ይሀንን ጽድቅ እንቀበላለን።

  ሮሜ 3:21–22

ፀጋ

- የሰው ልጆች ሀጢአት በጣም ብዙ ቢሆንም የወረደው ጸጋ ግን ከሀጢአታችንና ከበደላችን ሁሉ እጅግ በጣም የሚበልጥ ነው። ይህ ማለት ህግ በሀጢአት ምክንያት ከእኛ ሚፈልገው እዳችን በጣም ብዙ ቢሆንም ክርስቶስ የከፈለልን ዋጋ ከእዳችን እጅግ በጣም የበለጠ ነው።

ሮሜ 5:15-21

- በክርስቶስ ያመነ ሰው ስለ እዳው በህግ እንዳይጠየቅ ለህግ ሞቷል።

ሮሜ 7፥1–6

- ፀጋው ሀጢአተኛውን አድኖ ብቻ አያበቃም፣ አማኙ በመጨረሻው ዘመን ክርስቶስ ዳግም በመምጣቱ እና በስጋ ትንሳኤ እንዲቀበለው እስከተጠበቀለት ፍጹም ድነት ድረስ ይሄው ፀጋ አማኙን ሀጢአተኝነትንና አለማዊ ምኞትን ክዶ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየተጠባበቀ በዚህ ዘመን ራሱን በመግዛትና በጽድቅ፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንዲኖር ያስተምረዋል።

ቲቶ 2፥11–13 ፣ 1ኛ ጴጥ 1፡3-5

LAW vs Grace



UNDER WHICH ARE YOU LIVING?

ሕግ እና ፀጋ

ሕግ-አደለም የእግዚአብሔር ልጆች ልንሆን አገልጋዮቹ አንኳን እንዳንሆን ከልክሎን ነበር።

ፀጋው-ግን ሕይወትን ሰቶ ከባርነት አልፎ እስከ ልጅነት ክብር አደረሰን።

2 ቆሮ 3÷6

በሕጉ(ብሉይ)-የሚበሰብስ እንጀራ እና በልተውት የሚኖሩት ሳይሆን የሚሞቱበትን ሲሰጣቸው፡

በጸጋው(በአዲሱ)-ግን የሚያበላው የዘላለም የሕይወት እንጀራ የሚበላ ሆኖ ራሱ መጣላቸው።

ዮሐንስ 6 (John)48፤ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።49፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤50፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው።

ሕግ እና ፀጋ

በሕግ(በአሮጌው)-

አንዱ ድኖ ሌላው ሁሉ ይሞቱ ነበር፡

ለምሳሌ÷ ኖሕ እና ቤተሰቡ

ሎጥ(ሰዶም እና ገሞራ

በሕግ ዘመን ላለመሞት ሲኖሩ(ለሕጉ በሕጉ...

በፀጋ(በአዲሱ)-

2 ቆሮንቶስ 5

14፤..... አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ .....

እኛ ደግሞ ከዕርሱ ጋር ለመኖር ሞተናል...(ለፀጋ በፀጋ)

ሕግ እና ፀጋ

- እግዚአብሔር የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን።
  - ፊደል የሙሴ ሕግ ይገድላል መንፈስ አዲስ ኪዳን ግን ሕይወትን ይሰጣል። 2ቆሮ 3፡6
- ሕግ በሙሴ ዘመን ለእስራኤል ህዝብ ብቻ የተሰጠ።

ዮሐ 1፡17,ሮሜ 9፡4

- ♥ፀጋ በክርስቶስ ከዘላለም ዘመናት በፊት የተሰጠ።

2ጢሞ 1፡9-11

2 ጢሞቴዎስ 1 (2 ትኽመዐተሐየ)9፤ ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥

10-11፤ አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቶአል። እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል።

ሕግ እና ፀጋ

ሕጉ(ብሉይ ኪዳን)-

የሚበሰብስ~ጊዜያዊ~ቢቆይ እንኳን፡የሚሻግት፡ጊዜያዊ እንጀራን ሲሰጥ፡የኪዳኑን ጊዜያዊነት ያመለክታል።
ስለዚህ የምትደክም እና የማትጠቅም ናት።

ፀጋው(አዲሱ፤)፡-

የማይበሰብስ፣የማይበላሽ፣የማይጠፋ በልተውት ብርታትንና
ዘላለማዊነትን የሚያገኝኑበትን እንጀራ ሰጣቸዉ።

2ቆሮ 3÷11

ሕግ እና ፀጋ

- ሕግ የሞት አገልግሎት ነው።
- ❤ፀጋ የሕይወት አገልግሎት ነው።

2 ቆሮ 3፡7

- በሙሴ በኩል የተፈጸሙ ታምራቶች መካከል ውሀን ወደ ደም መቀየር ሲሆን ይህም የሞት አገልግሎትን ሲወክል
- ❤ጌታ ኢየሱስ ግን የመጀመርያ ተዐምራቱን ያደረገው ሰርግ ቤት ነው ውሃን ወደ ወይን በመቀየር ሰማያዊና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ እና ሕይወትን አስጀመረ።

ዩሐ 2 ,ዘፀ 7፡14-22

ሕግ እና ፀጋ

✍የሕጉ አገልግሎት በመጣበት ጊዜ 3000 ሺ ሰወች ሲሞቱ።

ዘፀ 32፡28

♥የሕይወት አገልግሎት ፀጋ ግን በባለ ሀምሳ ቀን ለ3000ሺ ሰወች ሕይወትን ሰቷል።

ሐሥ 2፡1-

✍ሕግ የኩነኔ አገልግሎት ሲሆን

♥ፀጋ የፅድቅ አገልግሎት ነው።

2 ቆሮ 3፡

✍ሕግ በክብር የነበረ

♥ፀጋ እጅግ በሚበልጥ ክብር የሆነ።

2 ቆሮ 3፡10

ሕግ እና ፀጋ

✍ሕግ እስራኤላውያን እና አባቶቻቸው ሊሸከሙት ያልቻሉት ቀንበር ነው።

ሐሥ 15፡10

❤ፀጋ ቀሊል እና የሚያሳርፍ ቀንበር ነው።

ማቴ 11፡28-30

✍ሕግን መስበክ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው

❤ፀጋ መስበክ ግን ለእግዚአብሔር መታዘዝ ነው።

ሐሥ 15፡19

ሕግ እና ፀጋ

- ሕግ ልብን የሚያውክ እና የሚያናውጥ አገልግሎት
- ፀጋ ከእግዚአብሔር ሰላምን ይሰጣል።

ሐሥ 15፡24, ሮሜ 5፡1-

- ሕግ የሀጢአት እና የሞት ህግ
- ፀጋ የሕይወት መንፈስ ህግ(መመሪያ)።

ሮሜ 8፡1-2

- ሕግ በክርስቶስ ፍፃሜ ያገኝ እና በአማኝ ላይ የተሻረ

ሉቃ 16-16

- ፀጋ ለዘላለም ፀንቶ የሚኖር ።

2ቆሮ 3፡11

ሕግ እና ፀጋ

✍ ሕግ ከሰወች ፅድቅን ይጠይቃል

❤ ፀጋ የተገለጠ የእግዚአብሔር ፅድቅ።

ሮሜ 10፡3-21

ሮሜ 3 (Romans)21፤ አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥

✍ሕግ ትእዛዝ ይሰጣል ነገር ግን ለሃጢያተኛው ሰው አቅም አይሰጥም።

❤ፀጋ ሲሰበክ ግን ቅዱሳን አቅም ያገኛሉ።

✍ሕግ አድርግ እና አታድርግ ሲል

❤ፀጋ ግን ተደርጎልሀል በማለት የምስራች ይናገራል።

ኤፌ1-1-10

ኤፌሶን 1 (Ephesians)3፤ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

ሕግ እና ፀጋ

✍ሕግ ራስህን እንድታይ ሲያደርግህ

❤ፀጋ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን ያሳያል።

ገላ 3፡1- ,4፡19

✍ሕግ ባሪያይቱ አጋር ልጆችንም ለባርነት የሚወልድ

❤ፀጋ ነፃይቱ ሳራ የሚወረሱ ጨዋ ልጆችን የምትወልድ።

ገላ 4፡21-31

✍ሕግ ወንጌልን ለሚቃወሙ ሰወች የተሰራ

❤ፀጋ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የሆነ።

1ጢሞ1፡8-11, ሮሜ 3፡24

☞ ሕግ ምድራዊ መቅደስ ከለከለን

❤ ፀጋ ግን ሰማይ ወደ ሰማያዊቱ ድንኳን ወይም ወደ አብ ቀኝ ከተተን

ሕግ እና ፀጋ

✍ሕግ ሰውን በማፅደቅ ደረጃ የምትደክም እና የማትጠቅም

❤ፀጋ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚሻል ተስፍ።

ዕብራውያን 7 (Hebrews)18-19፤ ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።

✍ሕግ አሮጌ እና ውራጅ

❤ፀጋ አዲስ።

ዕብ 8፡6-13

✍ሕግ ሃጢያትን ያስታውሳል

❤ፀጋ የዘለዓለም ፍፁም ያደርጋል። ዕብ 10

ዕብራውያን 10 (Hebrews)10፤ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።

14፤ አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።

Hebrews 10 (KJV) - ዕብራውያን14: For by one offering he hath perfected for ever them that are sanctified.

ሕግ እና ፀጋ

✍የሙሴ ሕግ ሲሰበክ ሃጢአት አቅም ያገኛል ሰውም የሀጢአት ተገዥ ይሆናል።

1ቆሮ 15፡56, ሮሜ 6፡14

(ሮሜ 6 (Romans)14፤ ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።)

♥ፀጋ ሲሰበክ ግን ቅዱሳን ሀይል በማግኘት ሀጥያተኝነትን እና አለማዊ ምኞትን በመካድ በፅድቅ እና በቅድስና ነፃነታቸውን ይለማመዱታል

(ቲቶ 2፡11-13, 1ቆሮ 15፡56)

✍ሕግን ና ኩነኔን አብዝቶ መስበክ ሞትን እንደመስበክ ነው።።

♥ፀጋ ሲሰበክ ግን ሕይወት ይበዛል ።

ሕግ እና ፀጋ

የጽድቅ አገልግሎት ማለት የተገለጠውን እና የእግዚአብሔር ፀጋ የሆነውን ክርስቶስን አብዝቶ መስበክ ማለት ነው።።

2 ጴጥሮስ 3 ፡ 18 ...በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

ሮሜ 1 (Romans)1-2፤ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።3-4፤ ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

LAW vs Grace



UNDER WHICH ARE YOU LIVING?

By Beimnet yalmzewd
Wcu 2012 EC
0964324390

GOD BLESSE YOU!!!

For any comment >>call 0964324390